# ጉድና ጅራት ከወደኋላ -የኢትዮሚዲያዉ ድብቅ አፍቃሬ ወያኔ ማንነት

ይህችን አጭር ማስታወሻ እንድጫጭር ያነሳሳኝ የኔዉ ያለፈ ጅልነት አይሉት ለአገር ሲሉ ሁሉን ወዳድነት እንደእግር እሳት የሚለበልብ ቁጭት ሰለተወብኝ ነዉ። በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ጹህፍ የመጀመሪያዬም ቢሆን፡ እልኬን ከማፈን እስቲ እንደኔዉ ላሉት የዋሆች የኢትዮጵያ ሚዲያ ታዳሚዎች ነቃ ጠንቀቅ ቢሉ ይህቺን ጥቆማ አቅርቢያለሁ።

ያዉ አንደልማዴ ድረ ገፆችን ቃኘት ቃኘት ሳደርግ በEthiomedia.com ላይ **ከፍተኛ የፖለቲካ ንቅናቄ በመቀሌ** የሚል ጹኅፍ http://www.ethiomedia.com/aurora/arena_mekelle.pdf. ቀልቤን ሳብ አድርጎኝ ዳር ከዳር አነበብኩት። ወደመደምደሚያዉ ገደማ **ጥቂት የወያኔ አመራር አባለት በፈጸሙት** ጥፋት አትወንጅሏቸዉ የሚል ከዚህ በታች ያለ አገላለጽ

> እራሳቸዉን ተቃዋሚ ነን ከሚሉ ኢትዮጵያዉያንም የትግራይ ሕዝብ ከሌላዉ ኢትዮጵያዊ ቢበልጥ እንጂ ያላተናነሳ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ ተረድተዉ ጥቂት የሕወሃት አመራር አባላት ባጠፉት ጥፋት በጅምላ ከመፈረጅ ልማዳቸዉ መቆጠብ እንዳላባቸዉ የሚናገሩት የፖለቲካ ተንታኞች፣ በመቀሌ የተደረገዉ ስብሰባ የከዚህ በፊት አመለካከታቸዉ የጠበበና የተሳሳተ ለነበሩ ሰዎች ትልቅ ትምህርጥ ሰጪ ነዉ ብለዉታል።

አየሁና ግራ ገባኝ፣ አይኔንም ማመን አቃተኝ ለምን ብትሉ ከድረ ገፁ የላይኛዉ ጫፍ የሚታየዉ **ወያኔ የሚሻሻል ሳይሆን መደምሰስ የሚገባዉ ኃይል ነዉ** የሚለዉ መርሃዊ ኃይለ-ቃል እኛን ለማጃጀል ካልሆነ በቀር በምን ስሌት ቢለካ ነዉ ወያኔ አላጠፈም ከጥቂት መሪዎቹ በሰተቀር ከሚለዉ ጋር ሊጣጣም የሚችለዉ። ይህን ያሰኘኝ በድረገፁ ላይ መዉጣቱ ብቻ ሳይሆን የዚህ የአቡጊዳ ዝግጅት ክፍለ ተብዬዉ ጹህፍ/ዘገባ አዘጋጅ ራሱ አብረሃ በላይ መሆኑን ማረጋገጤ ነዉ። የሚገርመዉ ድሮ ጋልበዉን አስጨብጨበዉን አገራችንን እየናዷት ሕዝቧንም እየጨረሱት ያለዉ ሳያንስ አሁንም በእኛዉ የዋህነትና ድጋፍ እኛኑ እያጋጩና እያባሉ ያሉት የሚዲያ ወኪሎቻዉ አንዱን ወያኔ በሌላ የመተካትና የትግራይ ነፃ አዉጭን የግዛት ዘመን የማራዘም ፕሮጀክታቸዉን እያከናወኑ ነዉ ለካ።

ከዚህ በኋላ ነበር ሌሎችንም የነስዬንና ገብሩ አስራትን ጹህፎች በቅጡ ማንበብ የጀመርኩትና የዛኑ የጎጠኛዉን አገር አጥፊ ሃሳብ አሁን በተቃዋሚ ስም እያራመዱ ያሉ መሆኑን የተገነዘበኩት። ለነገሩማ እኔ ዶከተሩ እንዲህ ከተሞኘሁ ሌላዉ ምን ይፈረድበታል።

በአሁኑ ስአት ወያኔን በትጥቅ ትግል መፋለም አይቻልም ከሚለዉ ቱልቱላቸዉ በተጨማሪ ለአብነትም ያህል በኢትዮሚዲያና በየነግንቦቶቹ ደጋፊ ድረገጾች ላይ ከወጡት ጹህፋቸዉ ዉሰጥ አንድ ሁለት አረፍተ-ነገሮችን ልብ በሉልኝ፣

የገብሩ አስራት *በኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥታዊ ሥርዓት አወቃቀር ላይ የሚነሡ ጥያቄዎች* ያንንኑ ኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ ያላት ናት የሚለዉን የወያኔ/ሸአቢያ ቀመር እንደሚከተለዉ በማስቀመጥ በጎንዮሽ አድርጎ ይደግመዋል፣

> ከአድዋ ጦርነት ድል በኋላ በሰሜን በኩል ከመረብ ጀምሮ በደቡብ በኩል እስከ ቦረና ድረስ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ የሚኒልክ ግዛት መሆናቸው ተረጋገጠ።

ዝቅ ብሎም የወያኔዉ ሽግግር መንግስት መሰረተ ሰፊ መሆኑን ሊያስረዳን ይዳደዋል፣ የሚቀጥለዉን ታዘቡልኝ፡

የደርግ ውድቀትን ተከትሎ የተፈጠረው የሽግግር መንግሥት አጀማመሩ ላይ ሰፋ ያለ መሠረት እንደነበረው ግን አይካድም።

በማያሻማ መንገድም ገብሩ አስራት በማጠቃለያዉ የሚከተለዉን በማለት ወያኔዉ አገር አጥፊ አይደለም ባሎ እንደገና ሊያጃጅለን ይሞክራል፡

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መሰረታዊ ችግር በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝምን በመከተል ወይንም ለመገንጠል መብት እውቅና መስጠ ያስከተለው ችግር አይደለም። የአብርሃ በላይ ጓድ ገብሩ ምን ልትሆኑ፡ አሁንም የማስጨበጭባችሁ እኔ እንደሆንኩ ያዉ ወያኔ ነኝ ይለናል።

ሌላዉ ወያኔ ስዬ አብርሃ አማካይ ስፍራ እንፍጠር የሚለዉ መጣጥፍ ደግሞ እንዲህ ብሎ ይጀምራል፤

በስልጣን ላይ ያለውን ወገን ለመቃወም ህጋዊ እውቅና አግኝቶ መንቀሳቀስ የተጀመረው የደርግ ስርዓት ከወደቀ በኋላ ቢሆንም ይህ እንግዲህ ሆዳሞችንና አስመሳይ ተቀዋሚዎችን በመቀበል እኛ ነን የመጀመሪያዎቹ ለማለት መሆኑ ነዉ። ለነገሩ ለእንዲህ ዓይነት ድራማ ደርግ እንደቀደማቸዉ እንደመኢሱን፣ ኢጭአት፣ ወዝሊግ፣ ማሌድ ያሉት ተቀዋሚ ተብዬ ምስክሮች ናቸዉ።

ስዬ ስለ 1997 ግንቦቱ ምርጫ ያዉ እንደመለስ/በረከት የህዝቡን ደምፅ በመፃረር የተባለዉን ነዉ የደገመዉ። ይህንንም አስመልክቶ ህዝቡ ከአዲስ አበባ ዉጭ ወያኔን አልጠላዉም ምክንያቱም ቅንጅት ያሸነፈዉ አዲሰ አበባ ብቻ ነዉ ለማለት የሚቀጥለዉን አስፍሯል፣ ባለፉት ሶስት

ምርጫዎች እንደታየው ግን በ97ቱ ምርጫ ቅንጅት አዲስአበባን ካሸነፈበት ክስተት በስተቀር በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ኢህአዴግን አሸንፎ ስልጣን ለመያዝ የበቃ ተፎካካሪ ፓርቲ አልተገኘም።

አለፍ ይልና እኛ ጀግኖቹ ያልገባንበት ትግል ግቡን አይመታም ወያኔም ስርአቱም አይደመሰስም ለማለት ደግሞ ቀጣዩን ይላል፤

ኢትዮጵያዊን በጋራ እምነቶችና ተስፋዎች ዙሪያ ተሰባስቦና ልዩነቶችንም አቻችሎ መሄድ ቀላል ፈተና እንደማይሆን ይገመታል።ይሁን እንጂ ሊያልፉት የማይቻል ፈተና አይሆንም።ይህንን ሳያሳኩ ኢህአዴግን የመተካትና በኢትዮጵያ ድሞክራሲን የማስፈኑን ዳገት መወጣት እንደማይቻል ደግሞ ሳይታለም የተፈታ ነው።

አሁኑ ያለዉ የፕሬስ ነጻነት በ1997ቱ ከነበረዉ ይሻሻል ለማለትና የታገዱትን ጋዜጦኞች ለማዉገዝ ልክ እነበረከት ነፃዉን ፕሬስ የወነጀሉበትን መንገድ በማስተጋባት እንደሚቀጥለዉ ይዘላብዳል፡

ይህም ሆኖ በዚህ ጨለማ ውስጥ የሚታይ ብርሃን አለ። አንድ ጎልቶ የሚታየው ብርሃን የመስከን ብርሃን ነው። ከጥላቻና ከስሜት የመውጣት በዚሁ ፈንታ በቁምነገር ላይ የማተኮር አዝማሚያ እየታየ ነው። ምርጫ 97 የነበረውንና ሁለት ሺ ላይ ያለውን ልዩነት አንድ ጋዜጠኛ በንፅፅር ሲግልጽልኝ « ምርጫ 97 ላይ ማስጮህ በጣም ተፈላጊ ነበር። ጋዜጣ መሸጥ ላይም ትልቅ አስተዋፅኦ ነበረው። አንድን ነገር ወስዶ ማስጮህ ከተቻለ ጋዜጣው ሰው ይገዛዋል። ሁለት ሺ ዓመተ ምህረት ግን ማስጮሁን ህዝቡ አይወደውም ይልቁንስ ስክን ያሉ በቁምነገር ለይ ያተኮሩ በመረጃ ላይ ያተኮሩ ፅሑፋችንና አምዶችን የያዙ ጋዘጦችን ነው አሁን ህዝቡ የሚገዛው አሁን ማስጮሁን እንደማይጠቅመን ስላየን በቁምነገር ላይ በተመረኮዙ ፅሑፎች ላይ እያነጣጠርን ነው»ነበር ያለው። ይሄ አንድ ምሳሌ ቢሆንም አሁን እየታየ ያለውን የሚገልፅ ምሳሌ

ይህንን እንግዲህ የነጻ ጋዜጦች ማህበርና ፀሀፉን እያስተናገዱለት ያሉት የሚዲያ ሰዎች ምን እንደሚሉ አላዉቅም፡፡

ስዬ በማያሻማ ሁኔታ ከታች ስለህገ-መንግስቱም ያስነበበዉ፣ ስብሃት ነጋ ባለፈዉ ጊዜ በፓቶልቶክ ቀርቦ ከደነፋዉ በምንም አይለይም፡፡

> ህገ መንግስት እንዳለንና በህገ መንግስቱ ዙሪያም የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሉን ይታወቃል፡፡ ያም ሆኖ በህገ መንግስቱ ውስጥ ያሉት መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ማስተካከል የሚቻለው በህገ መንግስቱ መሰረት ለስልጣን ከበቁ በኋላ ነው፡፡ ስለሆነም በህገ መንግስቱ ዙሪያ በተቃዋሚዎች መሀከል ልዩነት እንዳለና እነሱ የሚስተካከሉት ኋላ መሆኑን ተገንዝቦ እስከዛ ድረስ ግን በህገ-መንግስቱ መሰረት ህገ መንግስቱን አክብሮ መታገል እንደሚገባ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ላይ የስዬ ደጋፊዎች ግን የሰነበትን/የቆየን ተቀዋሚ ነን የሚሉት ምን እንደሚባሉ ለእኔ አይገባኝም፡፡ ቢያንስ ከላይ የጠቀስኳቸዉ ሃሳቦች እነርሱ የሚሉትን የሚቃረኑ ሰለሆነ ማለቴ ነዉ፡፡ የአሁኖችን የወያኔ ተለጣፊዎች ለመተካት የተኮለኮሉ ካልሆነ በስተቀር፡፡

እነገብሩና ስዬን ጠቀስ ያደረግሁት ስለእነርሱም ሆነ አሁን እነርሱን ሰማይ ለማዉጣት ወዲያ ወዲህ የሚሯሯጡትን ተቀዋሚ ተብዬዎች ጉዳይ ለመተንተን አይደለም፡፡ ይህንን በሳል የፖለቲካ ትንተናና ጥሩ የመፃፍ ችሎታ ያላቸዉ ይቀጥሉበት፡፡

ይልቁኑ እኔን ያነሳሳኝ እደግፈዉ የነበረዉ አብርሃ በላይ ድብቅ ወያኔያዊ ሴራዉ ነዉ፡፡ በሌላ አነጋገር እነሰዬና ገብሩን በመጥቀስ አብርሃ በላይ ላይ ያተኮረኩት ሰዉ ማን ይመስላል ቢሉ ወዳጄን ነዉና የነአረና ስዬን ሃሳብ ተቋዳሽ፣ አራማጅና ለዚህ ማስታወሻ ምክንያት የሆነኝ ፁህፍ አቅራቢ በመሆኑ ነዉ፡፡

ለካስ ተስፋዬ ገ/አብ የተባለዉ (የአሁኑ ከረንት አፌር ፓልቶክ ክፍል ታዳሚ) ወያኔ ስለ አብርሃ በላይ ያስቀመጠዉና በEthiopian review ድረገጽ ላይ ወጥቶ የነበረዉ ትክክል ነዉ፡፡ ቅንጫቢዉ እንደሚከተለዉ ይነበባል፡፡

> "እኛ" ወያኔዎች አዲሳባ በገባን ጊዜ እኔ ፕሬስ መምሪያ ሃላፊ ሆኜ ስመደብ፤ ፕሬስ መምሪያ ላይ በፈቃደኛነት ለወያኔ አባልነት ራሱን የመለመለ ቀዳሚው ሰው አብርሃ በላይ ነበር። "ጠላቶቻችንን" ከፕሬስ መምሪያ ስንመነጥር አብርሃ ዋናው ጠቋሚና መንገድ መሪያችን እንደነበር የፕሬስ መምሪያ ሰራተኞች በሙሉ የሚያውቁት ስለሆነ ይህ ምስጢር አይደለም።

ታዲያ ከሁሉም በላይ የሚቆጨኝ ከአንድ ጥሩ ወዳጄ ጋር የዚሁን ድብቅ ወያኔ በመደገፍ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የተቀያየምኩት ነዉ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነዉ፡ ብዙ ጊዜ ሌላ ድረ ገፅ የምሄደዉ በethiomedia በኩል ሰለነበረ ወደ debteraw ማገናኛዉ ተነስቶ አየሁና ለምንድነዉ ብዬ ወዳጄን ጠየቅሁት የመለሰለኝም፡ አብርሃ ማገናኛዉን ያነሳዉ፡ ደብተራዉ ላይ ዐረና ትግራይን የሚያጋልጥ ጹህፍ በአያልነሽ የወጣ ቀን፡ ተበሳጭቶ ነዉ አለኝ፤ (በነገራችን ላይ አንድ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር አንዱ መድረክ በጣም የሚወድና እንደእርጎ ዝንብ የማይገባበት የሌለ የእንገሊዝ አገር

ነዋሪ  ኢ.ኢ.ድን በሚባል የመወያያ መድረክ ይህንኑ የደብተራዉን ድረገጽ ማየት አቁሜአለሁ እናንተም እንደኔ ማለቱ አብረሃ በላይንና እምነቱን በመደገፍ ይሁን አይሁን ማወቅ እፈልጋለሁ)፤ እኔም አብረሃን በዚህ እጠረጥረዉ ሰላልነበረ አንተ ግራ የገባህ ነህ ብዬ ሙልጭ አድርጌ ሰደብኩትና እስከትናትና ይቅርታ ጠይቄዉ ሁኔታዎችን በግልፅ እስከተወያየንበት ጊዜ ድረስ አንነጋገረም ነበር፡፡ እኔ ጠርጣራ አለመሆኔ ነዉ እንጂ፡ ቀደም ሲል በጣም ብዙ ትችቶች በደብተራዉ ድረገፅ ላይ በወጡበት ጊዜ ማገናኛዉን ያላወጣ፡ ለምን እነገብሩ ተነኩ ብሎ ይህንን ርምጃ ሲወስድ በገባኝና ከጓደኛዬም ጋር ባልተቃቃርኩ ነበር፡፡

እንግዲህ የእኔ ምክር የዚህ ድረገጽ አዘጋጅ ተባባሪዎች እዉነቱን እያወቁ ነዉ ወይንስ በተተኪዉ የወያኔ መንግስት ተለጣፊ ለመሆን ማመልከቻ እያቀረቡ ይሆን፡፡ በተለይ ለረጅም ጊዜ የማቀዉ ጋሼ መስፍን (ፕሮፌሰር መስፍን) በእዚህ ላይ ምን አስተያት እንዳለዉ ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም የብርቱካንን ነገር አደራ የሚላቸዉ ቀደም ሲልም የኢሰመጉ ደጋፊ ኮሚቴ አባላት የነበሩ በአሜሪካም በእንገሊዝም ያሉ ግለሰቦች ከኢትዮሚዲያ ጀርባ መሆናቸዉን በሚገባ ስለማዉቅ ነዉ፡፡

በእኔ በኩል የእኔ ነገር አያሌዉ ሞኙ ሰዉ አማኙ ሆኖብኝ አጥፊዎቼን ስደግፍ በመኖሬ ትንሽ ቢፀፅተኝም በቅርቡ ለግንቦት ንቅናቄ ላስረክብ የነበረዉን አምስት መቶ ዶላር ለማዳን በመቻሌ ተደስቻለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህንን ለእኔ ብጤ የዋሆች ካካፈልኩ የድርሻዬን የተወጣሁ ይመስለኛል፡፡ ወደፊትም በስህተት ግትሮች፣ በጥባጮችና ትምህክተኞች እያልኩ ሳወግዛቸዉ የነበሩትን ሀቀኛ ፀረ ወያኔና የአንድነት ሃይሎችን ለመደገፍ ቃል እየገባሁ በዚሁ እሰናበታችኋለሁ፡፡

ኢትዮጵያን አምላክ ይጠብቅ!!!

ታደስ ቡላ (Phd)